www.fag.gov.et

የሰበር መዝ/ቁ. 19850

6/7/98

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- የደብረብርሃን ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- አቶ መኮንን አሠፋ

የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የተሠማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ከዚህ የሚተለውን ፍርድ ሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ያላግባብ የተሠናበቱ በመሆኑ የ3 ወር ደመወዝ ኪሣራ እንዲከፈላቸው በመወሠኑ ነው፡፡

ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ከሚሠሩበት ከአመልካች መ/ቤት በመሠናበታቸው ወደ ሥራ ለመመለስ በደብረ ብርሃን ወረዳ ፍ/ቤት ክስ መስርተው ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት የወሠነ ሲሆን ይግባኝ የቀረበለት ለሠሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን የክልሉን ማዘጋጃ ቤት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 መሠረት የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ቅሬታቸውን ለማቅረብ የሚችሉት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አዋጁን ተከትሎ በሚያወጣው ደንብ እንደሆነ ቢያመለክትም ይህ ደንብ ባለመውጣቱ የመንግስት ሠራተኛ አዋጅ ሆነ የአሠሪና

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 26/7/98

www.fag.gov.et

ሠራተኛ አዋጅ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የሌላቸው በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፍ/ሕጉ በመደበኛ ፍ/ቤት ነው በማለት የተጠሪ ስንብት ህገ ወጥ በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ. 2573 እና 2583 መሠረት የ3 ወር ደመወዝ ይከፈላቸው በማለት ወስኗል።

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለው በማለት ሲሆን ተጠሪ የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ሆነው የተሾሙ በመሆኑ ከሹመታቸው የመነሣታቸው ጉዳይ በፍ/ሕጉ መሠረት የሚዳኝ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቷል።

ተጠሪ በደብረ ብርሃን ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሆነው እንዲያገለግሉ በክልሉ መንግስት የተሾሙ መሆኑን በቃል ክርክር ወቅት አምነዋል። የተጠሪ ክርክር የሚያገለግልብት የአመልካች መ/ቤት የመንግስት መ/ቤት ባለመሆኑ ጉዳያቸው በፍ/ሕጉ መዳኘት አለበት በማለት ነው። ነገር ግን የደብረ ብርሃን አገልግሎት ጽ/ቤት የመንግስት ግብር በመሠብሠብ፣ መሬት ለሕዝብ በመስጠት እና የመሣሠሉትን የከተማው አስተዳደር ሥራ የሚሠራ መ/ቤት መሆኑን፣ ተጠሪነቱም ለከተማው አስተዳደር መሆኑን በቃል ክርክር ጊዜ ተጠሪ ገልፀዋል። እንግዲህ የአመልካች መ/ቤት ከሚያከናውነው ተግባር አኳያ የመንግሥት የሥራ አስፈፃሚ መ/ቤት መሆኑን መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ ተጠሪ በሥራ አስፈፃሚ መ/ቤት ለማስተዳደር በክልሉ መንግስት የተሾሙ ሥራ አስኪያጅ መሆናቸውን ፍ/ቤቱ ተረድቷል። የመንግስት ሹመኞች ከመንግስት ጋር ያላቸው የሥራ ግንኙነት ደግሞ በፍትሐብሔር ሕጉ የሚይዳኝ መሆኑ ከፍ/ህ/ቁ. 2513/1/ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም የሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመንግስት ተሿሚ የሆኑትን የተጠሪን ጉዳይ በፍ/ሕጉ መሠረት በመዳኘት ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት መሆኑን ተረድተናል።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 25/7/95

www.fag.gov.et

ው ሣ ኔ

1/ ተጠሪ በመንግስት የተሾሙ ባለሥልጣን በመሆናቸው ጉዳያቸው በፍ/ብሔር ሕጉ ሊዳኝ አይገባም።

2/ የሰ/ሸዋ ዞን መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5004 በ13/3/94 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.134/97 በ6/7/97 በሠጡት ውሣኔ ተሽሯል።

3/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ይ

